እርማት ሲሰጥህ በትሕትና ተቀበል

ዳዊት እና ቤርሳቤህ—ክፍል 2

መመሪያ፦ ይህን መልመጃ ጸጥታ በሰፈነበት ቦታ ሆነህ ሥራ። ጥቅሶቹን ስታነብ በቦታው እንዳለህ አድርገህ አስብ። ሁኔታውን በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል እንዲሁም በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች ሲነጋገሩ ድምፃቸውን ለመስማትና ስሜታቸውን ለመረዳት ሞክር። ታሪኩ ሕያው እንዲሆንልህ አድርግ።
ዋነኞቹ ባለታሪኮች፦ ዳዊት እና ናታን
ታሪኩ በአጭሩ፦ ዳዊት ለሠራው ከባድ ኃጢአት ምሕረት ቢደረግለትም ኃጢአቱ ያስከተለውን መዘዝ ከመቀበል ነፃ አልሆነም።

1 ሁኔታውን በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል ሞክር።—2 ሳሙኤል 12:1-24ን አንብብ።

ናታን ምን ዓይነት ባሕርይ ያለው ሰው ይመስልሃል?

ናታን ስለ ድሃው ሰውና ስለ በጉ የሚገልጸውን ምሳሌ ሲናገር ምን ዓይነት የድምፅ ቃና የነበረው ይመስልሃል?

ከቁጥር 7-9 ላይ እንደተገለጸው ናታን የምሳሌውን ትርጉም ሲናገር በድምፁ ቃና ላይ ለውጥ የሚኖር ይመስልሃል?

2 ጥልቅ ምርምር አድርግ።

ናታን፣ ዳዊትን ከማነጋገሩ በፊት በጉዳዩ ላይ አስቀድሞ በደንብ ማሰብ ያስፈለገው ለምን ሊሆን ይችላል?

ናታን፣ ዳዊትን ሲያነጋግረው ይህን ምሳሌ የተጠቀመው ለምን ይመስልሃል?

ናታን፣ ዳዊት ስለ ፍትሕ ያለውን ስሜት ከግምት እንዳስገባ የሚያሳየው ምንድን ነው? ዳዊት ጉስሐ እንዲገባ ለመጫን ከመሞከር ይልቅ እንዲህ ያለ ምሳሌ መጠቀሙ ይበልጥ ውጤታማ የሆነው ለምንድን ነው?

ይሖዋ፣ ዳዊትን ቶሎ ይቅር ያለው ይመስል ይሆናል። (*ቁጥር 13ን አንደገና አንብብ።*) ይሁንና ከሰዎች በተለየ ይሖዋ ምን ማየት ይችላል?

ዳዊት በሠራው ኃጢአት ምክንያት የደረሰበት ነገር ተገቢ እንደሆነ ይሰማሃል? ለምን? (*ቁጥር 10-12, 14ን አንደገና አንብብ።*)

www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

3 ከዚህ ታሪክ ያገኘሽውን ትምህርት ተግባራዊ አድርግ።

ከዚህ በታች ስለሰፈሩት ሐሳቦች ምን ትምህርት አንዳገኘህ ጻፍ፦

ስለ ትሕትና አስፈላጊነት _____

_____

ኃጢአት ስለሚያስከትለው መዘዝ _____

_____

ስለ ይሖዋ ምሕረት _____

_____

4 ራስህን ጠይቅ።

ምክር ወይም እርማት ተሰጥቶኝ የሚያውቀው መቼ ነው? _____

_____

እርማት ሲሰጠኝ ምላሽ የምሰጥበትን መንገድ ማሻሻል የምችለው በየትኞቹ መንገዶች ነው? _____

_____

ምክር ወይም ተግሣጽ ሲሰጠኝ ይህ ይሖዋ እንደሚወደኝ የሚያሳይ እንደሆነ አድርጌ ላየው የሚገባው ለምንድን ነው? (ፍንጭ፦ ዕብራውያን 12:5, 6ን አንብብ።)

_____

_____

ከዚህ ታሪክ የማገኘው ለእኔ በጣም አስፈላጊ የሆነው ትምህርት የትኛው ነው? ለምን?

_____

_____

ተጨማሪ ሐሳብ፦ ይህ ታሪክ ከዚህ የተለየ ፍጻሜ ቢኖረው ምን ሊሆን እንደሚችል አስብ። ዳዊት ጥፋቱን ባያምን አልፎ ተርፎም ናታንን ለመቅጣት ቢነሳ ኖሮ ታሪኩ ምን ዓይነት መደምደሚያ ሊኖረው ይችል እንደነበር ጻፍ። ዳዊት እንዲህ ቢያደርግ ኖሮ ይሖዋ በሰጠው ፍርድ ላይ ምን ለውጥ ይኖር ነበር?



JW.ORG™

ይህን ፒዲኤፍ ከwww.jw.org/am ላይ ማውረድ ትችላለህ

www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania